## ጥላሁን ገሠሠ ከኛ ጋር ሞተ!፡ እኛም ከጥላሁን ጋር ተቀበርን!

ከዘነበ በቀለ

የተወዳጁና ታዋቂው አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ዜና ዕረፍት በእርግጥም በሙያው ውስጥ ያለውን ሰው ሁሉ ስሜት የነካ አልፎም በማህበረ ሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤን የፈጠረ ነው። ጥላሁንን ብዙዎቹ እንደገለፁት ታላቅ ያደረገው የዘፈኖቹ ግጥሞች ብቻ አልነበሩም። ከዚህ ውጭ የሆኑ የጥላሁንን ሀያልነት የሚመሰክሩ ሙያዊ ብቃቶች አሉ። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሙዚቃ በተለይም ሰሜነኛው ወይም ዜማ ተኮር በሆነው ክፍል ትልቁ መለኪያ ቅላፄ ነው። በአንድ መሰረታዊ ድምፅ ላይ እንደሻሽ የሚጠመጠሙ ኖታዎች መኖር ሙዚቀኛውን ፈተና ውስጥ የሚጥሉ ናቸው። እነዚህ በራሳቸው ሪትም የመቆም ባህርይ የሌላቸው ኖታዎች በጥላሁን ዘዴ ተፈጥሮላቸዋል። ለምሳሌም ፈረንጆች “አፖጂአቱራ” እና “አካቺአቱራ” በሚል የሚገልፁአቸው ኖታዎች ከዜማው መሰረታዊ መነሻ ፊት ቀድመው በመሰረታዊው ዜማ ሪትም ውስጥ ተጠቃለው የሚገለፁ ናቸው። ብዙውን ጊዜ እንኳንስ በድምፅ በመሳሪያም ቢሆን ለሪትም አስቸጋሪዎች በመሆናቸው ባውሮጳውያኑ ሙዚቃ ውስጥ ከክላሲካል ሙዚቃ ድርሰት ውጭ አልፎ አልፎ ነው የተስተዋሉት።

በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ ግን በተለይም “Textual” በሆነው የሙዚቃ አይነት ከቃላቱ እኩል ዋጋ ያለው አጅቦ የሚገለፀው ቅላፄ ነው። ይህ የአጨዋወት ዘይቤ ለብዙ ዘማሪዎች አስቸጋሪ ነው። ጥላሁን ይህንን ያለምንም ችግር ወደላይ (ascending) እንዲሁም ወደታች (decending) ፎርም ያላቸውን የቅላፄ ዜማ ባህርያት የማካተት ችሎታ ያለው የሙዚቃ ሰው በመሆኑ እነዚህን አስቸጋሪ እርከኖች በድምፁ ለማለፍ ብቁ ችሎታ ያለው ነበር። ጥላሁን ድምፅን በራሱ አዘማመር ስልት ውስጥ ለማገር ከፍተኛ ጥረት ያደረገና የተሳካለትም ባለሙያ ነበር። በእርግጥ በመጀመሪያዎቹ በክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ውስጥ ባደረጋቸው ቅድመ ልምምዶቹ የተካነ በመሆኑ በሁዋላ የመጡት ዜማዎች ሁሉ ለሱ እምብዛም አስቸጋሪ አልነበሩም። ለምሳሌ “እንጉዳዬ ነሽ” የሚለው ዜማ ድርሰቱና ቅንብሩ የሌሎች ቢሆንም ከራሱ ከጥላሁን የተጨመረ እንደ “interlude” የሚያገለግል “ጭር” የሚል ድምፅ አለ። ይህ አይነቱ አሰራር ለመሳሪያ ተጨዋቾቹ የሚተው ቢሆንም ጥላሁን ግን የመሳሪያ ተጫዋቾቹንም ስፍራ ሞልቶ የመጓዝ ችሎታ የነበረው ዘማሪ መሆኑን ያስመሰከረበት ነው። ከዚህ ውጭ ጥላሁን የዜማውን ባህርይ የሚከተልና በቅላፄ የተሞላ ተጫዋች በመሆኑ ለሪትም አጠባበቅ ከፍተኛ ችግር እንደሚገጥመው ይስተዋል ነበር። ያም ሆኖ ግን ይህንን አስቸጋሪ እርከን ለማለፍ የፈጠረው ዘዴና የተቀናጀ አሰራሩ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ባለሙያ አድርጎታል።

ለዚህ ሁሉ የሙያ ብቃቱ አስተዋፅኦ ያደረጉትን የሙያ ጓዶቹን እነ ፅጌ ፈለቀን ገዛኸኝ ደስታን፤ እነ ኮሎኔል ሳህሌ ደጋጎን፤ እነ ተዘራ ሀይለሚካኤል፤ ብዙነሽ በቀለን እና ሌሎችንም ሳይጠቅሱ ማለፍ አግባብ አይሆንም። ጥላሁን መሰረታዊ የሆነውን የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት አሰራር ስልት ከነ አቶ እዩኤል ዮሃንስ ያጠና በመሆኑ ከነተስፋዬ ለማ ዜማ ድርሰት የቀሰመ በመሆኑ” ከነካሳ ክራር ድርድር የተቃኘ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሙዚቃ አሰራር ስልት የተዋሃደው ሰው ነበር። “ብርቱካኔ“ የሚለው ዜማው ድምፁን ከተፈራ ካሳ አኮርዲዮን ጋር አዋህዶ ሲቀርብ ልምድ የቀሰመበት እንደሆነ ግልፅ ነው። “ዘንድሮ” የሚለውን የአቶ ተስፋዬ ለማን ዜማ ብንመለከት ለጥላሁን የሙዚቃ ስልት መንገድ ከፋቹ እንደሚሆን መገንዘብ እንችላለን። ወደ ዘመናዊነት እየተለወጠ ለመጣው ያቀራረብ ስልቱ የአቶ ሰሎሞን ተሰማ ድርሰት የሆነው “አትመልከቺ ሱፍ” የተሰኘው ሙዚቃ በር ከፋቹ እንደሆነ እንረዳለን።

Ethiopia will prevail !

ጥላሁን በክብር ዘበኛ የሙዚቃ ጓድ ታጅቦ በሚሰራበት ጊዜና በሁዋለኛው ዘመን ከሌሎች ባንዶች ጋር የተጫወታቸውን ማመሳከር ይቻላል። በክብር ዘበኛ ሙዚቃ ላይ መሳሪያዎች እየተከተሉ ከስር ከስሩ የሚሰጡት ድጋፍ ጥላሁን የዜማ ማረፊያውን በኩራት እንዲያረጋግጥ የሚረዱት ናቸው። ጥላሁን እራሱም እንደሚገልፀው ቅብጥብጥ ስለሆነ በዜማው አይረካም ሁልጊዜ አዳዲስ ድምፆችን ለመጨመር ይጥራል። ለዚህ አሰራሩ የሚረዳው ደግሞ የክብር ዘበኛ አይነት የጃዝ ሙዚቃ ድርሰት እንደሆነ ይታያል። ምክንያቱም አቀነባበሩ በጋራ ትስስር ላይ ያተኮረ በመሆኑ ድማፃዊውና ሙዚቀኛው አንዱ የአንዱ መንገድ ጠቋሚ ሆነው ነው የሚያገለግሉት። ከጊዜ በሁዋላም በታዋቂው ጋዜጠኛ በአቶ ጳውሎስ ኞኞ ተደርሶ የተሰጠውን "ዋይ ዋይ ሲሉ" የሚለውን ዜማ አሳምሮ የመጫወት ክህሎቱ እየረቀቀ መምጣቱን አረጋግጧል። ጥላሁን ከህዝብ ጋር በቅርበት የኖረ ሰው በመሆኑ ጭምር ያካበተው ጥበብ ፍሬያማና መንገዱም ቀላል ሆነለት። ዋናውና ትልቁ ግን ጥላሁን ለሙዚቃ የነበረው ፍቅር ሀያልነት በመሆኑ፤ ብዙ ውጣ ውረዶችን በፅናት እንዲቋቋማቸው አድርጎታል። በመጨረሻው የህይወት ዘመኑ ላይ የደረሰበት ጉዳት ሁሉ በህዝብ ላይ ቀድሞ የደረሰ በመሆኑ መሸከም አልተሳነውም። የኪነጥበብ ሰዎች ባብዛኛው ከሞቱ በሁዋላ ነው ጥቅማቸውም ሆነ ጉዳታቸው የሚታወቀው። የጥላሁን ገሰሰንም ሆነ የሎሬት ፀጋዬን ሞት ምሬት እያጣጣምነው ያለነው በተተኪነት ሊመደቡ የሚበቁ ባለሙያዎችን የማፍራቱ አቅም ከኛ የራቀ መሆኑን ስንገነዘብ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ መንግስታት የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ኪነጥበብን የሙጠኝ ስለሚሉ ለዚህ ተግባራቸው አልንበረከክም የሚሉ የኪነት ሰዎች ዕጣቸው፣ ሀገራቸውን ትተው መሰደድ፣ ከሙያው ተለያይተው መኖር፣ የመሳሰሉት ስለሚሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት ሀገራችን ከርሞ ጥጃ ሆናለች ማለት ይቻላል። የሙዚቃው ደራሲ አሸናፊ ከበደ ህይወቱ የጠፋው በባዕድ አገር ሳለ ነው። ደራሲ ተስፋዬ ለማ በህመም ላይ የሚገኘው በባዕድ አገር ነው። እነዚህ ሰዎች በራሳቸው ህይወት ላይ ከደረሰባቸው አደጋ ውጭ አላማቸው ትልማቸው ያለተከታይ የቀረበት ሁኔታ ነው የሚስተዋለው።

ፒያኒስት ግርማ በየነ ከሙያው አደባባይ ሲጠፋ ጀምሮት የነበረውን መስመር የሚገፋበት አልተስተዋለም። እነ ተሾመ ምትኩ፣ እነ መልካሙ ተበጀ፣ አያሌው መስፍን፣ እነ ሻምበል በላይነህ፣ እነ ጠለላ ከበደ፣ ሌሎችም በእናት አገር ፍቅር እየተሰቃዩ ያሉት ሁሉ፣ በህይወት በሚኖሩበት ሰዓት ተተኪ አፍርተው ለማለፍ የሚያስችላቸው መንገድ ባለመኖሩ ነው ሀዘናቸው። ካሳ ተሰማ የክራርን አጨዋወት ዘዴ በተለይም የንድፍን አሰራር፣ ጎን ለጎን ከአስናቀች ወርቁ ጋር በመሆን ያስፋፋና ያስተዋወቀ ሰው ቢሆንም መንገዱና ዓላማው ተጨናግፎ ከራሱው ጋር ተቀብሮ ቀርቷል። ካሳ ክራሩ ብቻ ሳይሆን በእንጉርጉሮ ውስጥ በወፍራም ድምፅ ጀምሮ ያለምንም (ቮይስማስኪንግ ቴክኒክ) በወፍራም ድምፅ ዜማን የመጨረስ አስቸጋሪነትን የተወጣ ጥበበኛ ዘማሪ ነበር። ይህ አይነቱ ጥበብ ብቸኛ የሆነ የካሳ ንብረት ነው ቢባል ማገነን አይሆንም። የአስታጥቄ መንገሻን የክራር ግርፍ በቀጣይነት ይዞ ሲንቀሳቀስ የነበረው ተሾመ ደምሴም በህይወቱ ክልል ውስጥ ብቻ ተርጉሞት አልፏል። ለዘፋኞች የሚሆን የድምፅ ስኬልን በመምረጥ ረገድ የሚታወቀው ተዘራ ሀይለሚካኤል እንኳንስ ዕውቀቱ ሊተላለፍ እሱም ተቸግሮ ያለፈ እንደሆነ ይታወቃል። በኳየር አዘማመር ስልት የበለፀገ ልምድ የነበራቸው ሙሴ ነርሲስ ናልባንዲያን ያለምንም ቀጣይነት ጥበቡ እዚያው ላይ እንዲያከትም ሆኗል። የሴትነት ድርብ ድርብርብ ጭቆናዋን ገመድ በጣጥሳ የወጣቻው ብዙነሽ በቀለም በርካታ ዘመናዊ ሴቶችን ወደ ሙያው እንዲገቡ መንገድ ትክፈት እንጂ! የቀሰመቻቸው ልምዶች ለሌሎች እንዲተላለፍ አልሆነም።

በዚህ ረገድ ስንመለከተው ጥላሁንን ልዩ የሚያደርገው ነገር የለም። ያወቀውንና ያለፈባቸውን ዘዴዎች ሁሉ ለተከታዮቹ ዘማሪያን የሚያስተላልፍበት ዕድል አልነበረውም። ዕድለኛነትን የቀባሪ ብዛት አይለካውምና ጥላሁን የተለየ ዕድለኛ ነው ማለት አይቻልም። ይህ ለዘመናት የለፋባቸው ጥበባዊ ቴክኒኮች ተመዝግበው ለትውልድ መጠቀሚያነት እንዲያገለግሉ መሆን ይገባቸዋል። በስሙም የዘማሪዎች የድምፅ ጥናት ትምህርት ቤት እንዲከፈትለት ያስፈልጋል። ይህን መሳዩ የትውልድና የሀገር ቀጣይነት ራዕይ ተግባራዊ እንዲሆን የሙያ ማህበራቱ ቆርጠው ካልታገሉ፣ በየጊዜው በሚወድቁ አባላት መቃብር ላይ ያበባ ጉንጉን ከማኖርና፣ መንግስታትን እየተማፀኑ መወደስ ከመደርደር ያለፈ ስራ ላይሰራ ይችላል። ያ! ከሆነ ደግሞ ጥላሁን ገሠሠ ከኛ ጋር ሞተ!፡ እኛም ከጥላሁን ጋር ተቀበርን! ብንል ስህተት አይሆንም። ፈጣሪ! የወንድማችንን የጥላሁንን ነፍስ ይማርልን!! አሜን!!

EthioLion.Com